# ★ ዴሞክራሲያ ★

* የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ልሳን *

## የኢሕአፓ 36ኛ ዓመት ምስረታ በዓልን አስመልክቶ የወጣ

**ልዩ ዕትም** **ነሐሴ** 2000


## ትግላችን ቀጥሏል

*ታሪካዊው የየካቲት 1966 ዓም የኢትዮጵያ አብዮት ከተጀመረ ይኸው 34 ዓመታት አስቆጥሮ 35ኛውን እያገባደደ ነው፡፡ ይህ ዘመን ከረዥሙ የሀገራችን ታሪክ አኳያ ሲነፃፀር ኢምንት ነው ለማለት ቢቻልም፥ የአንድ ትውልድ ዕድሜ አስቆጥሮ ወደሚቀጥለው ትውልድ በመሸጋገር ላይ የሚገኝ መሆኑ ግን የሚታበል አይደለም፡፡ አንድ ትውልድ ለሀገሩ ፍቅርና ለወገኑ ክብር ሲል፥ ይኸ ነው የማይባል መሥዋዕት የከፈለበት ወቅት በመሆኑ በሀገራችን የታሪክ ሂደት ሲገመገም ቀላል ዘመን አይደለም፡፡ በተለይም ዓለም በየደቂቃው በሚያስደንቅ ፍጥነት በሳይንስና ቴክኒዮሎጅ እየተለዋወጠና ገፅታውን እየቀየረ ባለበት ወቅት፥ 35 ዓመታት እንዲያው በአርምሞ ሊታይ የሚገባው ዘመን አይሆንም፡፡ የዓመታቱ መለዋወጥም እንደ ተፈጥሮ ህግ በቻ ተቆጥሮ እንዲያው በተለምዶ ይነጋል-ይመሻል በሚል መጽናናት ሊታለፍ የሚቻልም አይደለም፡፡ በ35 ዓመታት የትግል ሂደት የተከፈለው መሥዋዕትና የተመዘገበው ብሔራዊ ውጤት ሲነፃፀር፥ መሳ ለመሳ ነው ለማለት አያስደፍርምም፡፡ 35 ዓመታት አንድ ህፃን ተወልዶ አድጎ ለአካለ-መጥን ደርሶ ልጅ በመውለድ ለወላጆቹ የልጅ ልጅ የሚያበረክትበት ዘመን ነው፡፡ በዚህ ስሌት ከተሄደ ደግሞ በቅድመ-የካቲት የነበረው ትውልድ ለተተኪው ትውልድ ሀገሩን የሚያስረክብበት ዘመን ሊሆን ነው፡፡ ያ ትውልድ በበኩሉ ምን ዓይነት ሀገር ነው የማስረክበው? የትኛዋን ኢትዮጵያ ነው ለተረካቢው ትውልድ የማስተላልፈው? እኔስ ምን ዓይነት ሀገር ነበር የተረከብኩት? በየካቲት አብዮት ማግስት የማውቃትን ሀገር፥ ኢትዮጵያን እንደ ሀገር፥ ዜጎቿንም እንደ አንድ ሀገር ሕዝብ ለማስረከብ እችላለሁ/ችያለሁ? ያ ካልሆነስ ለዚህ ተጠያቂው ማን ይሆናል? የሚሉና ሌሎችም ተዛማጅ የሆኑ ጥያቄዎችን ማንሳቱ አይቀርም፡፡ ጥያቄዎችን እየጠየቀ ትክክለኛውን መልስ የማግኘት መብት ደግሞ የተተኪው ትውልድና የታሪክ አንጡራ ሀብት እንደሆነ ሁሉም ሊገነዘበው ይገባል ፡፡*

*በነኝህ 35 ዓመታት ሀገራችን በከፍተኛ የለውጥ ማዕበል ሂደት አልፋለች፡፡ በዚህም የለውጥ ማዕበል ሦስት ሥርዓቶች ተፈራርቀዋል፡፡ የተፈራረቁበት ሁኔታ ግን ተተኪው ዋና ሥራ አድርጎ የሚይዘው፥ የጣለውን ሥርዓት የሚያስንቅ አዲስ የተሻለ ሥርዓት መመሥረት ሳይሆን፥ ለከፋና ለከረፋ አገዛዝ መጣል ነው፡፡ በአለፉት 35 ዓመታት፥ ገዥዎችና ጨቋኞች በሚያራምዱትና ተፃራሪ ክፍሎች በፈጠሯቸውና ባካሄዷቸው ከፍተኛና ንዑሳን አውዳሚ ጦርነቶች፥ ዕልፍ አዕላፍ ዜጎቿ ተመትረዋል፡፡ ግምቱ በትክክል የማይታወቅ ብሔራዊ ሀብት-ንብረት ወድሟል፡፡ ከሀብት ንብረቱ፥ ከሀገሩና ከወገኑ፥*

የተፈናቀለውን ዜጋ ቤቱ ይቁጠረው ከማለት በስተቀር፥ ይህን ያህል ይሆናል ብሎ ምናልባታዊ ግምት ለመስጠት የሚደፍር አይገኝም፡፡ የነዋሪዎቿ ቁጥር ከግማሽ በላይ አድጓል ቢባልም፥ የሀገሪቱ የቆዳ ስፋት ግን ተጨማትሯል፡፡ በቅድመ የካቲት 66 ዓም የነበረው ዳር ድንበሯ ጀርት እንደበላው ዱባ ተቦርቡሯል፡፡ የዜጎቿ ክብር ተዋርዷል፡፡ የኢትዮጵያም ሉዓላዊነት፥ ተደፍሯል፡፡ ሀገራዊ የግዛት ልዕልናም ይሁን የሕዝቦቿ አንድነት በየጊዜው እየተፈረፈረ ከመሄድ የሚያቆመው ማዕከላዊ ኃይል አልተገኘም፡፡ የረሀቡና የጠኔው ክፋትና ብርታት አሁንም እየቀጠለ እንጅ እየቀነሰ አይደለም፡፡ የበሽታውን ዓይነትና ብዛት፥ የሥራ አጡንና የድህነቱን መጠን፥ እዚህ ደረጃ ነው ብሎ ለማለት የሚቻል አይደለም፡፡ በዘርና በጎጥ ተከልሎ እንዲወሰን የሚደረገው አዲሱ ትውልድ፤ የኢትዮጵያዊ ዜግነትና ኅላዊ እየተነፈገው በማደግ ላይ ስለሆነ በማንነት ፍለጋ ላይ እየባዘነ ይገኛል፡፡ ለአንድ ትውልድ ደግሞ የማንነት ፍለጋ ለማግኘት ከመጨነቅ የበለጠ የሀገር ጥፋት ምልክት አይኖርም፡፡ ምክንያቱም ከኢትዮጵያዊ ዜግነት ማንነትህ ይልቅ የጎሳህና የዘርህ መለያ ቅድሚያና አጽንዖት ሊሰጠው ይገባል ተብሎ በዘር በሽታና መርዝ እየተጋተ ስለሚያድግ ነው፡፡ በሃያ አንደኛው ምዕተ-ዓመት ጅማሮ ላይ ጥንታዊቷ ኢትዮጵያ፥ ዜጎቿን በዘርና በቋንቋ ከፋፍሎ ለመግዛት መሞከር ኋላ ቀር አስተሳሰብ ብቻ ሳይሆን፥ የኢትዮጵያን ሕዝብ ታሪክና ባኅል ካለማወቅ አልፎ ተርፎ፥ የአዕምሮ ብስለቱንና የማሰብ ችሎታውንም ጭምር መፈታተንም ነው፡፡ይህ ሙከራ ካለማወቅ የመነጨ የድንቁርና ድፍረት መሆኑን አለመረዳት የወያኔ መሪዎች፥ የቱን ያኅል ጥላቻና ንቀት ያላቸው መሆኑን ያመለክታል ተብሎ የሚታለፍ ብቻ አይደለም፡፡ ከዚህ በላይ አልፎ ተርፎ፥ ኢትዮጵያን እንደ ሀገር፥ ዜጎቿንም እንደ ሕዝብ መኖር የለባቸውም ብለው የቆየ ዕቅዳቸውን ለማስፈፀም ተግተው ሲሰሩ ለኖሩ የቅርብና የሩቅ የሀገራችን ጠላቶች ኅልም ማስፈፀሚያ አገልጋይ የሆኑት የወያኔ መሪዎች ጠንክረው የሚሰሩት የሥራ ድርሻ ነው፡፡ ይህንን ሐቅ በአሁኑ ወቅት የማይገነዘብ ኢትዮጵያዊ ይኖራል ተብሎ አይታሰብም፡፡ የሀገራችንን ሁለንተናዊ የፖለቲካ፥ የኢኮኖሚና የማኅበራዊ መልከዐ-ምድር ለማማተር ስንሞክር፥ ከማንኛውም በፊት ልናጤነው የሚገባን በወያኔና በተቀዋሚው መካከል ያለውን ሁኔታ መገምገም እንዳለብን ነው፡፡

የተወሰነው በሞቅ ሞቅ የሕዝብ ድጋፍ ያገኘ የመሰለው ክፍል የወያኔን ማንነትና ምንነት በሚገባ ከአለማወቁ የተነሳ፥ በየጊዜው ከነመለስ ዜናዊ በሚወረወርለት የመንቀሳቀሻ አጀንዳ ላይ ብቻ በማተኮር፥ ሰሞናዊ ግርግር እየፈጠረ እርስ በእርሱ ከመራኮትና ከመጠላለፍ አልፎ ተርፎ ያመረቃ የትግል ውጤት ሊያሳይና ሊያስመዘግብ አልተቻለውም፡፡ የአመራር ችሎታውንም ከነባቢት አልፎ፥ በድርጊት አስመዝግቦ ለማስመሰከር ከቶ አልሆነለትም፡፡ በራስ አነሳሽነት የራስን የትግል አጀንዳና የአሰራር ስልት ፈጥሮና አዳብሮ ዘረኛውን አገዛዝ ከማስጨነቅና ከማርበትበት ይልቅ፥ ለወያኔ ድርጊትና ምግባር ምላሽ በመስጠት ብቻ በመወሰን፥ የትግሉ ማዕከላዊ ይዘትና እንቅስቃሴ ሲያደርገው ቆይቷል - በአመዛኙ፡፡ ከወያኔ የሚወረወረው የቤት ሥራ አጀንዳ ለጊዜው ጋብ ሲል ደግሞ፥ ሁሉም ሁኔታና ሂደት ፀጥ ረጭ ይላል፡፡ መኖርን ለማሳወቅ ሲባል ደግሞ ሌላ ከወያኔ የሚመረወረውን  የአገዛዙ  ዕቅድ እንዲከሰት ይጠበቃል፡፡ በኢትዮጵያ ሕዝብ የትግል እንቅስቃሴና በተቃዋሚው ጎራ መካከል ያለው ክፍተት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየሰፋና እየተራራቀ መሄድ እንጅ ሲቀራረብ አይታይም፡፡ ይኸም ሁኔታ የፖለቲካ ተቃዋሚው ክፍል ሚና ምን እንደሆነ እንኳ በቅጡ ሊታወቅ አልተቻለም፡፡ የኢትዮጵያን ሕዝብ የትግል ንቃተ ህሊና በሚገባ ተረድቶ ለሚከታተለው  ነፃ የፖለቲካ ተንታኝና ወገንተኛ ያልሆነ አርቆ አስተዋይ ዜጋ፥ ማን መሪ ማንስ ተመሪ እንደሆነ የራሱን ፍርድና ድምዳሜ ከመውሰድ የሚሳነው አይደለም፡፡

ይኸም አጠቃላይ ክስተት ቢያንስ እራሳቸውን የ  ሉ ሁለት ምክንያቶች አሉት፡፡ የመጀመሪያው፥ ሁለት የአመለካከትና የአቋም ልዩነቶች መኖራቸው ነው፡፡ አንደኛው ወገን ወያኔ የኢትዮጵያ ሕዝብ ጠላት አይደለም፡፡ በመሆኑም የወያኔን የራሱን ሕገ "መንግሥት" አምኖና ተቀብሎ፥ በብሔረሰብ አወቃቀር ላይ የተመሠረተውንም ፌደሬሽንና አፈፃፀሙን ደግፎ ካስፈለገም ጥገናዊ ለውጥ እያደረጉ ከወያኔ ጋር አብሮ ለመስራት የወሰነው ወገን ነው፡፡ የዚህ አቋም ተፃራሪ ደግሞ፥ ወያኔ የኢትዮጵያ ሕዝብ ቋሚ ጠላት በመሆኑ በእርሱ ምክንያት ሀገሪቱ ከመጥፋቷ በፊት ወያኔን አስወግዶ ኢትዮጵያን ማዳን ቅድሚያ የሚሰጠው የትግል መርህ ግብር መሆን አለበት ብሎ የተነሳና ለሥርዓት ለውጥ ቆርጦ የሚታገል ኃይል ነው፡፡ ሁለቱ አቋሞች ያገጠጡ ያፈጠጡ ተፃራሪ አቋሞች በመሆናቸው በተቃዋሚው ጎራ መካከል የሰከነ ውይይት ተደርጎ የጋራ ስምምነት ሊደረስ እስካሁን

*አልተቻለም፡፡ይህ ክስተት ደግሞ፥ በትግሉ ስልት፥ ዘዴና አካሄድ ሆነ ዘላቂ ግብ ላይ የአቋም ልዩነትን አስከትሏል፡፡ ለጥገና ለውጥ የቆመው ክፍል ወያኔን መታገል በሰላምና በህጋዊ መንገድ ብቻ ነው ብሎ ራሱን በራሱ ሸብቦ ሲደይን፥ ለሥርዓት ለውጥ የሚታገለው ደግሞ፥ ይኸንን ዘረኛ አገዛዝ ታግሎ መጣል የሚቻለውና የሚገባው በሁለገብ ትግል ብቻ ነው በማለት የትግሉን አድማስና ምርጫ እያሰፋ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ፍላጎትና ውሳኔ ጋር እያገናዘበ መታገል አለብን ይላል፡፡ ከሁለቱ ተፃራሪ አቋሞች የኢትዮጵያ ሕዝብ የትኛውን መርጦ እንደሚወስን ሳይታለም የተፈታ በመሆኑ፥ ይህ ነጥብ በአሁኑ ወቅት ለክርክር የሚቀርብ ሆኖ አልተገኘም፡፡*

*ከዚህ ከሁለት ከተከፈለው የአቋምና የአመለካከት ተፃራሪ ልዩነት ባሻገር፥ በሁለተኛ ደረጃ ሊታይ የሚገባው፥ የሀገራችን የቅርብና የሩቅ ባላንጣዎች የሚጫወቱት አፍራሽና የደመኝነት ሚና ነው፡፡ ሀገራችን በታሪኳ የቅርብ መልካም ጎረቤትም ይሁን የሩቅ አዛኝ ወዳጅ እንደሌላት የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚያወቀው ሐቅ በመሆኑ በዚህ ክስተት ላይ ብዙ ማለት ላያስፈልግ ቢችልም፥ የወቅቱን ሁኔታ በምንዳስስበት ወቅት ግን በግድ መወሳት የሚገባቸውን ነጥቦች ሳንጠቁም ማለፍ አንችልም፡፡ የውጭ ኃይሎች ለረዥም ዘመን በኢትዮጵያ ላይ ያላቸውን ፖሊሲ በሥራ ለመተርጎም አመች ጊዜ የተፈጠረላቸው፥ በወያኔ ዘመነ መንግሥት ነው፡፡ ለዚህም ነው ወያኔን ሥልጣን እንዲይዝ የረዱት፥ በሥልጣን ላይ እንዲቆይም ተከላካይ የሆኑለት፡፡ የሀገራችን ምንነት ለባዕዳን መስህብ መሆን ተደጋግሞ ተደጋግሞ የተገለፀ ነው፡፡ የሀገራችን ተፈላጊነት በብዙ ረድፍ ታይቶ ተገምግሞና ታምኖበት የቆየም ጉዳይ ነው፡፡ ከቅድመ-ቅኝ ግዛት ጀምሮ እስከዛሬ ድረስ በተላያዩ ሁኔታዎችና አጋጣሚዎች ሲታዩ የነበሩ ክስተቶች ለዚህ ምስክር ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ በመሆኑም የዜጎቿ አንድነት፥ የነፃነቷ ፍጹምነትና ሆነ የግዛቷ ሉዓላዊነት ተጠብቆ እንዲኖር የሚፈልጉ አይሆኑም፡፡ ሀገር ወዳድ ዜጋና መንግሥት እንዲኖር የሚፈልግ የቅርብም ይሁን የሩቅ ኃይል ሊኖር አይችልም፡፡ ምዕራባውያን ደግሞ ከሁሉ በላይ የሚጠሉት በኢትዮጵያ ሀገር ወዳድ የሆኑ መሪዎች መኖራቸውን ነው፡፡ ይህ እንዳይከሰት ማድረግና የራሳቸውን ጥቅም ግን የሚጠብቅላቸውን አሻንጉሊት ቡድን ማቆየት የግድ ይሆናል፡፡ ለዚህም ከወያኔ የበለጠ ሲጠሩት አቤት ሲልኩት ወዴት የሚል ታማኝ አሽከር ፈጽሞ ሊያገኙ እንደማይችሉ አበክረው ተረድተውታል፡፡ በመሆኑም፥ ወያኔን አስወግዶ በምትኩ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ዴሞክራሲ ለማምጣት የሚታገለውን ቆራጥና ዕውነተኛ ሀገር ወዳድ ኃይል ሁሉ በኢትዮጵያ የፖለቲካ መልከዐ-ምድር ፈጽሞ እንዳይመጣ የተቻላቸውን ሁሉ ከማድረግ የሚቆጠቡ አይሆኑም፡፡ ለዚህም ነው የተጠናከረ የተቃዋሚ ኃይል እንዳይኖር ለአለፉት አስራ ሰባት ዓመታት ከፍተኛ መሰናክል ሲያደርጉ የቆዩት፡፡ የመረጃ ሰዎቻቸውንና ታማኞቻቸውንም በአንዳንድ የተቃዋሚ ድርጅቶች ውስጥ ሰርስሮ በማስገባት ኢትዮጵያን የማዳከሙን ተልዕኮ የሚያስፈጽሙትም ከዚህ ዘላቂ ጥቅማቸውን ከማስጠበቁ አኳያ እያዩት ለመሆኑ ማንም ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያዊ የሚስተው አይደለም፡፡*

*ያም ሆኖ ግን እኛ ኢትዮጵያውያን የባዕዳን ጠላቶቻችንን ጥቃትና ደባ ብቻ እንደ ዓይነተኛ ሰበብ እየተመረኮዝ፥ ለራሳችን ድክመት መሸፈኛና ማጠየቂያ ልናደርገው የሚገባን ሊሆን አይገባም፡፡ ጠላቶች ሊያጠቁን የሚደፍሩንና ሊያዳክሙን የሚችሉት ለጥቃታቸው መግቢያ ቀዳዳ ሲያገኙ ብቻ እንደሆነ ለማንም ስውር ሊሆን አይችልም፡፡ የተቃዋሚው ክፍልም ሆነ ጠቅላላው የኢትዮጵያ ሕዝብ በመሠረቱ ለውጭ ባዕዳንም ይሁን፥ ለሀገር ውስጥ ጠላቶች ሰለባ ለመሆን የሚበቃው፥ የራሱን ኅብረትና አንድነት ስስ ብልት አጋልጦ ሲሰጥ ብቻ እንደሆነ መጠቆሙ፥ ችግሮቹን ሁሉ አቃልሎ እንደማቅረብ ብቻ ሊቆጠር የሚገባው ነው ብለን አናምንም፡፡ ባዕዳንና የሀገር ውስጥ ተባባሪዎቻቸው በሀገራችን ላይ የሚያደርጉት ጥቃትና ጉዳት እንደተጠበቀ ሆኖ፥ አሁን ለተከሰተው የሀገራችን ፖለቲካዊ፥ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ውስብስብ ችግሮች ብሎም፥ መንስዔዎችና ምክንያቶች ሁሉም በየፈርጁ ኃላፊነት እንዳለበት ሊገነዘበው የሚገባው ሀገራዊ ዕውነታ ነው ብለን እናምናለን፡፡ ይህንን ኃላፊነት ተቀብሎ ብሔራዊ መፍትኄ ለመፈለግ መጣር ችግሮቹን ለማስወገድ በሚደረገው ሂደት እንደ መጀመሪያ እርምጃ የሚቆጠር የብሩኅ ተሰፋ ምልክትና የአቅጣጫ ተቋሚ ውጋገን መሆኑን እንገነዘባለን፡፡ ለተግባር መመሪያችን በቅደም ተከተል ሂደት የሚያስፈልገንን ግንዛቤ ማግኘት ከተሳነን፥ "የራሱን ህይወት በገዛ እጁ እያጠፋ ትንሳዔን እንደሚጠብቅ" ዜጋ እንዳንቆጠር ማስተዋል አለብን፡፡ ይህንን መሠረታዊ ኃላፊነትና ግዴታ ከእኛው ከራሳችን ከኢትዮጵያውያን/ት ራስ እንደማይወጣ በሚገባ ተገንዝበን፥ የሀገራችንን የፖለቲካ መልከዐ-ምድር እኛው ራሳችን መቆጣጠር*

እስካልቻልን ድረስ፥ እንዳንቆጣጠር ምክንያት በሆኑት የውጭና የውስጥ ጠላቶች ዙሪያ እየተሽከረከርንና ከነባቢት ያላለፈ ተቃውሞ በማሰማት ላይ ብቻ ከተወሰን፥ ሀገር እናድናለን ማለት ዘበት ይሆናል።

የዛሬዋ ዓለማችን ተጨባጭ ሁኔታ በትክክል ሊያስረዳን የሚሞክረው፥ የነዋሪዋ ቁጥር በአስደንጋጭ ፍጥነት እየጨመረ፥ የተፈጥሮ ሃብቷ እያደር እየቀነሰና እየነጠፈ፥ ለሰው ልጅ ህይወትና ኑሮ አስፈላጊ የሆኑት ማንኛቸውም አቅርቦቶች እየተመናመኑ መሄዳቸውን ነው። ይህ ደግሞ ምዕራባውያንን ያልተነካና ያልተዳሰሰ የተፈጥሮ ሃብት ወደ አላቸው ሀገሮች በማተኮር ፍላጎታቸውን ሊያረኩበት የሚያስችላቸውን ሁሉ ለማድረግ የሚከለክላቸው ኃይል እንደሌለ በሚገባ ያውቁታል። በዚህ ረገድ፥ ሀገራችን ኢትዮጵያ የመጀመሪያውን መስመር ይዛላቸው እንደምትገኝ በትክክል ከተረዱት ቆይተዋል። ሀገራችንን ለምዕራባውያን ዐይንና ቀልብ፥ የህብት ስስትና መጎምጀት መስኅብ የሆነችበት ምክንያት የሁለንተናዋ ማንነቷ ነው። በመሬቷ ላይ ያለው የተፈጥሮ ሃብቷ ገና ያልተላሰ ያልተቀመሰ ነው።

የኢትዮጵያ መልከዐ-ምድራዊ አቀማመጥ ጥቅማቸውን ለሚያስቀድሙ በወታደራዊ ኃይልና በኢኮኖሚ ለዳበሩ አገሮች ሁነኛ ቦታና ስትራተጂያዊ ዕምብርት በመሆኑ፥ ሀገራችንን ምዕራባውያን መራኮቻና ፍልሚያ ሰለባ አድርጓት ቆይቷል። ይህ ክስተት አሁንም እንደቀጠለ ይገኛል የዚህ መቀጠል ደግሞ በከፋና አስቸጋሪ በሆነ መልኩ ሆኗል። ከቀዝቃዛው የዓለም ጦርነት ማክተሚያና የቀድሞዋ ሶቨሺዬት ኅብረት ከከሰመች በኋላ፥ ዓለም በአሃዳዊ ልዕለ ኃይል መዳፍ ወድቃለች። ይህ ብቸኛ ኃይል የዓለም ሀገሮችን በጠቅላላው፥ የሦስተኛ ዓለም የሚባሉትን ሀገሮችን ደግሞ በተለይ ለመቆጣጠር የሚያስችለውን ሁኔታ ለራሱ እንዲመቸው በራሱ ዕቅድና ሂደት እያስተካከለ በመጓዝ ላይ ይገኛል። የራሱን አሻንጉሊትና ቅጥረኛ አምባገነኖችንም በየሀገሮቹ ሥልጣን ላይ እያስቀመጠ የራሱን ብሔራዊ ጥቅም ማስጠበቂያ አገልጋይ እያደረጋቸው ይገኛል። ለዚህ ክስተት እንደ ጉልህ ማስረጃና ተጨባጭ ምሳሌ የምትጠቀሰው በዘረኞቹ በነወያኔ አገዛዝ ስር የወደቀችው ሀገራችን ኢትዮጵያ ለመሆኗ ጥርጥር ሊኖር አይችልም። ዛሬ ይህ ልዕለ ኃያል፥ በሀገራችን እንደ ወያኔ ያለ ሲጠሩት አቤት ስልኩት ወዴት የሚል ታማኝ አገልጋይ ስላለው የኢትዮጵያ ሕዝብ ከዘረኞች አገዛዝ ለመላቀቅ የሚያደርገውን ትግል በዝምታ የሚመለከተው አይሆንም። ወያኔን አስወግዶ የኢትዮጵያን ሀገራዊ ጥቅም የሚያስጠብቁ ሀገር ወዳድ መሪዎች እንዳይተኩ ማንኛውንም ዘዴ እየተጠቀመ ያሰናክላቸዋል። ለአለፉት አስራ ሰባት የትግል ዓመታት የተፈፀሙት ደባዎችና ድርጊቶች ለታሪክ የሚጠቀሱ ናቸው።

ይህም በመሆኑ፥ ሀገራችንን ከዘረኞች አገዛዝ ነፃ በማውጣት እነርሱንም አስወግዶ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ለመመስረት የሚደረገውን ትግል በተመለከተ ፈፅሞ አይቻልም የሚል ጨለምተኝነት ይኖራል ተብሎ ባይታሰብም፥ ፍልሚያው ግን ቀላል አይሆንም። ይህንን ተገንዝቦ አዲስ የትግል ስልትና አሰራር በመቀየስ ትግሉን ማፋፋም የወቅቱ የሀገራችን ሁኔታ የሚያስገድደው ብቻ ሳይሆን የኢትየጵያ ሕዝብ ውሳኔም ጭምር መሆኑን ኢሕአፓ ያምንበታል። ከዚህ መሠረታዊ ሐቅ በመነሳት፥ አዲስ የትግል ምዕራፍ ለመክፈት ከመጀመሩ አስቀድሞ የትግል አጋሮቹንና ባላንጣዎቹን በየፈርጁ ለይቶ ማወቅ ወሳኝነት አለው። የመጀመሪያው ተግባር፥ ከላይ ከፍ ብሎ ለመጠቆም እንደተሞከረው፥ ለሥርዓት ለውጥ የሚታገሉትንና ለውሽልሽል ጥገና የሚፍጨረጨሩትን ለይቶ ማወቅ ያስፈልጋል። የወያኔን ድክመት እየጠጋገንን፥ የጎደለውን እያሟላን፥ አብረን በመጓዝ፥ በሚቀጥለው የወያኔ ምርጫ የሚሰጠንን የወንበር ድርሻ እያገኘን እንቀጥል የሚሉት በአንድ ወገን ሲፈረጁ፥ የወያኔን የዘር አገዛዝ አስወግዶ በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መተካትና ኢትዮጵያንም ከጥፋት ማዳን የትግላችን አልፋና ኦሜጋ ነው ብለው በመነሳት ለሥርዓት ለውጥ የቆሙ ኃይሎች በሌላ ወገን ቆመዋል። የዚህ የኃይል አሰላለፍ መኖር ደግሞ አዲስ ክስተት አይደለም። ታሪክ በተለያየ ወቅትና አጋጣሚ ራሷን ትደግማለች እንደሚባለው፥ ከደርግ ጋር ለመተባበር የፈለጉ ክፍሎች፥ ግራውን እያጠናከርን ቀኙን እያዳከምን ሂሳዊ ድጋፍ መስጠት እንችላለን ሲሉ እንደነበረ የሩቅ ጊዜ ትዝታ አይደለም። መጨረሻቸው ምን እንደነበረ ሁሉም የሚያውቀው ነው። ክፉ መካሪ ሕዝብ አስመታሪ፥ ፀላዒ ሰናያት፥ አምሳለ አጋንንት፥ ነውና ደርግም ከነአማካሪዎቹ የዶግ አመድ ሆኖ ቀረ። የኢትዮጵያ ሕዝብም በበኩሉ "ይብላኝ ለእናንት እንጅ፥ እኔስ ይኸው አለሁ"፥ እያለ የሰቆቃ ኑሮውን ይገፋል።

*የሰቆቃና የመከራው ፅዋ ሞልቶ ሲገነፍል ግን የኢትዮጵያ ሕዝብ አመፅ እንደ አሳተ-ጎሞራ ከፋፋዮቹንና ብሔራዊ ጠላቶቹን አቃጥሎ እንደሚፈጃቸው የየካቲት ስድሳ ስድስቱ ሕዝባዊ አመፅ ታሪክ ህያው ምስክር ነው:: ታዲያ ዛሬም እንደ ትላንትናዎቹ ሁሉ÷ የወያኔን ብሔራዊ ወንጀል ለመሸፈንና ብሎም ዘረኛ አገዛዙ መልኩን እየለዋወጠና ሀገር የማጥፋቱንም ሂደት በበለጠ የሚያጣድፍበትን ሂደት እንዲያራምድ የሚያስችለውን ሁኔታ ለማመቻቸት መለስን እየመከርንና በምርጫውም እየተሳተፍን እንሂዳለን የሚሉ ክፍሎች ዋናው ተልዕኳቸው÷ የኢትዮጵያን ሕዝብ የነፃነት ትግል ተፋፍሞ ዳግማዊ የካቲት እንዳይመጣ ለማድረግ ለመሆኑ ምንም ብዥታ ሊኖር አይችልም::*

*ይህንን የሕዝብ አመፅ ለማኮላሸት የሚደረገውን የውስጥና የውጭ ሴራ÷ ከተመሠረተ 36 ዓመት በይፋ ከታወጀ ደግሞ 33ኛ ዓመቱን በነሐሴ 26 ቀን የሚያከብረው ኢሕአፓ በበኩሉ በቅርብ እየተከታተለ የሚያጋልጠውና የሚታገለው እንጅ በቸልታ የሚመለከተው እንዳልሆነ÷ ያሳለፋቸው የሠላሳ ስድስት ዕመታት መሥዋዕታዊ ተጋድሎዎች ህያው ምስክሮቹ ናቸው:: ይህ ፍንክች የማይል ብሔራዊ አቋሙን ይዞ ለመቀጠል የቻለበትም በሁለት መሠረታዊ ምክንያቶች ነው:: የመጀመሪያውና ዓይነተኛው ምክንያት÷ ከጥንት ከጧቱ ፓርቲው ሲመሰረት ጀምሮ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር የገባው የትግል ቃል-ኪዳንና በዚህም ቃል ኪዳን ላይ ተመርኩዞ የሚታገልበት የዕምነት ፅናቱ ነው:: በመሆኑም ሰማይ ዝቅ መሬት ከፍ ቢል ይህንን የዕምነት ፅናቱን አይለውጥም:: ታማኝነቱም ለህገሩ ለኢትዮጵያና ለሕዝቦቿ ብቻ ነው:: ለግል ጥቅም÷ ወይም ለጊዜያዊ ምቾት ብሎ የቃል-ኪዳን ዕምነቱን በማጉደል ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጠላቶች ጋር የሚደራደር ፓርቲ አይደለም:: ሁለተኛው ምክንያት ደግሞ የፓርቲውን ብሔራዊ ዓላማና ሀገራዊ ራዕይ አንግበው በፅናት ሲታገሉ የተዋደቁት ሰማዕታት ጓዶቻችን የትግል አደራ ስላለብን ነው:: የኢትዮጵያ ሕዝብ ደግሞ በአኩሪ ታሪኩና በአስመስጋኝ ባህሉ÷ አደራ ጠባቂና ቃሉን አክባሪ ልጆቹን ስለሚወድና ስለሚደግፍ÷ ይህም ለፅናታችን ድርና ማግ ሆኖ አቆይቶናል:: ለአንድ ታጋይ ድርጅት÷ ከዚህስ የበለጠ ምን የመንፈስና የአዕምሮ ጥንካሬ ሊገኝ ይችላል? ይህንን ሁለንተናዊ ጥንካሬ መሠረት ያደረገ ታጋይ ድርጅት÷ ከሚደግፈውና ከሚተባበረው ሕዝቡ ጎን በመቆም ትግሉን እያፋፋመና ትግሉም የሚጠይቀውን ማንኛውንም መሥዋዕት በመክፈል የመጨረሻው አቸናፊ ከመሆን የሚገታው አንዳችም ኃይል አይኖርም::*

*ፓርቲው የተመሠረተበትን 36ኛ ዓመትና ፓርቲው የታወጀበትን 33ኛ ዓመት ስንዘክር የኢሕአፓ አባላትና ደጋፊዎች ሁለት ተደራራቢ ስሜቶች በአዕምሯችን እንደሚላወሱብን እንገነዘባለን:: አንደኛው የሀዘንና የሰቆቃ ስሜት ነው:: ይህ የቁጭት ስሜት የመጣው÷ ሀገራችን ኢትዮጵያ አሁን የገጠማትን የህልውና አደጋ ከማየትና ምንስ መደረግ አለበት ከሚል ሀገራዊ መቆርቆር ሲሆን÷ ሁለተኛው ደግሞ÷ ለፍትኅ-ርትዕና ለዴሞክራሲ መምጣት ሲባል ዕልፍ አዕላፍ ሰማዕታት ኢትዮጵያውያን ሕይወት የጠየቀው ትግል እስከ አሁን ግቡን ካለመምታቱ የመነጨ መሪር ሀዘንና ቃጠሎ ነው:: ይህ እንዳለ ሆኖ ግን ትግላችን በብሩኅ ተስፋና በዘላቂ ራዕይ ላይ የተመሠረተ በመሆኑ÷ የትግሉ መርዘም÷ የመስዋዕቱ መክበድ÷ የሀገራችን ጠላቶች መረባረብ÷ ዓላማችንንና የትግል ቃልኪዳናችንን ሊለውጠውና አቅጣጫውንም ሊያስተው አለመቻሉን በማወቃችን የትግላችን መሠረት የሆነውን ኢትዮጵያውነታችንን ተላብሰን እስከ መጨረሻው ምዕራፍ የምንታገል መሆናችንን ስለምናውቅ ነው:: በአንድ ሀገር የታሪክ ሂደት ደግሞ የመከራና ደስታ መለዋወጥ÷ ያልተለመደ ክስተት ባለመሆኑ÷ እኛን ሊያስገርመን የሚችል አይደለም:: ስለሆነም የጀመርነውን ግብ ሳናይ ትግላችንን የምንገታ አንሆንም::*

*ኢሕአፓ ዛሬ በሠላሳ ስድስት ዓመታት የትግል ዕድሜው ውስጥ ያሳለፋቸውን ውጣ ውረዶችና የከፈለውንም መሥዋዕት ሲገመግም÷ ምን ጊዜም ቢሆን የዘመን መለዋወጥም ይሁን የሁኔታዎች መገለባበጥ ሊሸሩት የማይችሉትን የዓላማውን መቅድም እንደገና እያስረገጠና እያደሰ መታገሉን ያሰምርበታል:: ይህ የዓላማው መቅድም ምንድን ነው? የፓርቲው ዓላማ መነሻና መድረሻውማ÷ የኢትዮጵያ ሕዝብ÷ ሉዓላዊነትና የሥልጣን ምንጭነት በሕግ የሚረጋገጥበት÷ በዜጎች እኩልነት ላይ የተመሰረተ÷ የሕዝብና የሀገር አንድነት የሚጠበቅበት÷ የሃሳብ የዕምነትና የኅሊና ነፃነት የሚከበርበት÷ በሕዝብ ነፃና ርትዓዊ ምርጫ የሚቋቋም ፌዴራላዊ ሪፑብሊክ መመስረት ነው:: ይህንን*

***ተግባራዊ ለማድረግ ከሚያስችሉት የማዕዘን መሠረቶች፥ የዲሞክራሲያዊና የሰብዓዊ መብቶች መረጋገጥ መሆኑ አንድና ሁለት አይባልም፡፡ እነኝህ እንዲጠነክሩ ዋስትና የሚሆነው ደግሞ፥ አሳታፊ ዴሞክራሲን ማበልፀግ ይሆናል፡፡ የዚህ አውደ ራዕይ ዕውን መሆን፥ የፓርቲው የአባላት እምነትና ግብ፥ የትግላቸው ዕርካታ፥ የመስዋዕታቸው ሕያውነት፥ የሰማዕታቱ ዘለዓለማዊነት የሀገራቸውና የሕዝባቸው የድል አክሊል መሆኑን ያምኑበታል፡፡ አባላቱ፥ ለምንና ለማን እንደሚታገሉ ስለሚያውቁና ግልፅ የሆነ ራዕይም ስላላቸው፥ የዓለም አቀፍ፥ የአካባቢና የሀገር ውስጥ ሁኔታዎች እንደፈለጉት ቢለዋወጡና ቢገለባበጡ በፅኑ መሠረት ላይ የተገነባውን ዓላማቸውን ሊያናውጠው ቀርቶ ሊያወዛውዘው ከቶ አይችልም፡፡ የትግላችን የማዕዘን ድንጋይ፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ ብሔራዊ ጥቅምና የሀገራችን ዘለዓለማዊ ህልውና በመሆኑ፥ የዓላማ ፅናታችንንና ቃል ኪዳናችንን ጠብቀን ከመታገል የበለጠ ደስታና ክብር ሊኖረን አይችልም፡፡***

**ትግላችን ይቀጥላል**!!